# ለኦሮሚያ ባንክ ባለአክስዮኖች የተደረገ
# የስብሰባ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ እና 370፤ እንዲሁም በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 14(5) መሰረት፤ የኦሮሚያ ባንክ (አ.ማ) የባለአክሲዮኖች 15ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኞ ታህሳስ 7 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊንየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 1. ባንኩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

**1.1.** የባንኩ የተፈረመ ካፒታል፤......... 7,461,545,000

**1.2.** የባንኩ የተከፈለ ካፒታል፤........... 6,550,408,000

**1.3.** የባንኩ ምዝገባ ቁጥር፤.........KK/AA/3/0007345/2007

**1.4.** የባንኩ አድራሻ፤ አዲስ አበባ፣ ክ/ከተማ፣ ቂርቆስ፣ ወረዳ፣ 01 የቤት ቁጥር፤ 407

## 2. የ15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

**2.1.** እስከ ታህሳስ 6 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የተፈፀሙ የአዳዲስ አክሲዮኖች ሽያጭና የነባር አክሲዮኖች ዝውውርን መመልከት፣

**2.2.** እ.ኤ.አ የ2023/24 የዳይሬክተሮች ቦርድን የሂሳብ ዓመት ሪፖርት ማዳመጥ፣

**2.3.** እ.ኤ.አ የ2023/24 የሂሳብ ዓመት የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ማዳመጥ፣

**2.4.** የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣

**2.5.** የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣

**2.6.** የ2023/24 የሂሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈልን አስመልክቶ በቀረበው የውሣኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

**2.7.** እ.ኤ.አ ለ2024/25 በጀት ዓመት የሚያገለግሉ የውጭ ኦዲተሮችን ሹመት ማጽደቅና አበላቸውን መወሰን፣

**2.8.** እ.ኤ.አ የ2024/25 የዳይሬክተሮች ቦርድን ወርሃዊ አበል እና እ.ኤ.አ በ2023/24 ባንኩ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ለቦርዱ የሚሰጥ ዓመታዊ ጉርሻ(Compensation) ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

## 3. ማሳሰቢያ

**3.1** የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**3.2** በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በኢፌዲሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያቸው በሚገኙ የባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በቦርዱ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉት የቦርድ አባላት ወይም የባንኩ ሰራተኞች ለሌሎች ባለአክስዮኖች ወኪል በመሆን በጉባዔው ላይ መሳተፍ አይችሉም፡፡

የኦሮሚያ ባንክ (አ.ማ)

የዳይሬክተሮች ቦርድ

አድራሻ፡ ዋና መ/ቤት፣ አፍሪካ ጎዳና ኦሎምፒያ አካባቢ፣ ለበለጠ መረጃ ስ.ቁ 011-557-21-09